አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

ቁጥር 24, ሚያዚያ 2015 ዓ.ም Issue No. 24, April 2023

# አዋሽ ዜና መጽሔት
# Awash Newsletter

በማርኬቲንግና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የሚታተም
Published by: Marketing & Communication Directorate

ዋና አዘጋጅ: ተሾመ ዋቅጅራ
ረዳት አዘጋጆች: ሰላም ተክለጽዮን
ድሪባ መገርሳ
ጋዲሳ አስፋው
ሲሳይ ነዳ
ዲናኦል ዱጋሳ
ጫልቺሳ ገመቹ
ግራፊክስ: ጋዲሳ ቶሌራ
ፎቶግራፍ: ዳንኤል ምትኩ

EDITOR-IN-CHIEF: Teshome Wakjera
ASSISTANT EDITORS: Selam Tekletsion
Deriba Megerssa
Gadisa Asfaw
Sisay Neda
Dinaol Dugasa
Chalchisa Gemechu
PHOTOGRAPHER: Daniel Mitiku
Graphics: Gadisa Tolera

8980
12638
www.awashbank.com
contactcenter@awashbank.com

# በዚህ እትም

አዋሽ ባንክ ለአዋሽ ብር ተጠቃሚዎች የታማኝነት ነጥብ የሚያስገኝ መርኃ ግብር ተግባራዊ አደረገ.......1
አዋሽ ባንክ የ2022/23 የመጀመሪያው መንፈቅ ሂሳብ ዓመት የሥራ አፈጻጸም ግምገማ አካሄደ.......2
አዋሽ ባንክ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ.......6
አዋሽ ባንክ በቦረና ዞን በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች 30 ሚሊዮን ብር ለገሰ.......8
አዋሽ ባንክ በተለያዩ የሀገራችን ከተሞች አዳዲስ ህንጻዎችን ሊገነባ ነው.......8
እፍታ.......15

# IN THIS ISSUE

Proverbs.......17
Quotes.......18
Photo Reel.......20

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# አዋሽ ባንክ ለአዋሽ ብር ተጠቃሚዎች የታማኝነት ነጥብ የሚያስገኝ መርኃ ግብር ተግባራዊ አደረገ




አዋሽ ባንክ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ያለውን የሞባይል ባንኪንግ አገልግሎት ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ እና የደንበኞችን ፍላጎት የተሟላ ለማድረግ (Loyalty point Incentive Program) ከየካቲት 22 ቀን 2015 ዓ/ም ጀምሮ ይፋ አድርጓል፡፡

ባንኩ ይፋ ያደረገዉ የታማኝነት ነጥብ ማበረታቻ ፕሮግራም ደንበኞች አዋሽ ብርን ተጠቅመዉ ማንኛዉንም ክፍያዎች እና ግብይቶችን ሲፈፅሙ የዚህ ዕድል ተጠቃሚ እንደሚያደርጋቸው ተገልጿል፡፡

የባንኩ ተጋልጋዮች አዋሽ ብርን በተጠቀሙ ቁጥር ማለትም ገንዘብ ሲያስተላልፉ፣ግብይት ሲፈፅሙ፣የአየር ሰዓትን ሲገዙ፣የትምህርት ቤት ክፍያን ሲፈፅሙ፣የዲኤስ ቲቪ እና የካናል ፕላስ ክፍያን ሲፍፅሙ እንደሁም አዋሽ ብርን ለተለያዩ አገልግሎቶች ሲጠቀሙ ነጥብ የሚያሰጥና ነጥቡም ተጠራቅሞ ለሽልማት የሚያበቃና ሽልማቱም በአየር ሰዓት መልክ የሚሰጥ ልዩ የማበረታቻ ሽልማት የሚያገኙበት መሆኑን በመግለጫው ላይ ተጠቁሟል፡፡

አዋሽ ባንክ በአሁኑ ሰዓት ከ825 በላይ በሆኑት ቅርንጫፎቹ ከ9 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ደንበኞች አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኝ ሲሆን ደንበኞችም ባሉበት ቦታ ሆነው ማንኛዉንም የባንክ አገልግሎት በተሟላ ሁኔታ እንዲያገኙ የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ተደራሽ አድርጓል፡፡

የባንኩ አጠቃላይ የሞባይል ባንኪንግ ተጠቃሚ ከ5 ሚሊዮን በላይ ከመድረሱም ባሻገር በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ የአዋሽ ብር ሞባይል ባንኪንግን በመጠቀም እንዲዘዋወርና ባንኩ ይህንን አገልግሎት የሚጠቀሙ ደንበኞችን ለማበረታታት ከዚህ ቀደም ሁሉንም አገልግሎቶች ሲጠቀሙ የአገልግሎት ክፍያን ነፃ ከማድረጉ በተጨማሪ አሁን ደግሞ የበለጠ የዲጂታል ባንኪንግ ተጠቃሚን ለማበረታታት በተጠቀሙት አገልግሎት ሁሉ የማበረታቻ ሽልማቱ እንዲካተት አድርጓል፡፡

# አዋሽ ባንክ የ2022/23 የመጀመሪያው መንፈቅ ሂሳብ ዓመት የሥራ አመራር ስብሰባ አካሄደ




የመጀመሪያ መንፈቅ ሂሳብ ዓመት የሥራ አመራር ስብሰባ በከፊል

አዋሽ ባንክ በ2022/23 ሂሳብ ዓመት የመጀመሪያው መንፈቅ ዓመት ላይ በተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እና ባጋጠሙ ችግሮች ላይ በመወያየት እና በቀሪው የሂሳብ ዓመት መከናወን በሚገባቸዉ ተግባራት ላይ በመመካከር ቀጣይ አቅጣጫዎችን ለማስቀመጥ የመጀመሪያው መንፈቅ ሂሳብ ዓመት የሥራ አመራር ስብሰባ ጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም በስካይ ላይት ሆቴል አካሂዷል፡፡

የአዋሽ ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ፀሐይ ሽፈራው ስብሰባውን በመክፈቻ ንግግር የከፈቱ ሲሆን በንግግራቸዉም በመጀመሪያው መንፈቅ ዓመቱ በዓለምና በሀገራችን በተከሰተዉ የፖለቲካ አለመረጋጋት የዋጋ ግሽበት በእጅጉ እንዲጨምርና የውጭ ምንዛሪ ዕጥረት በከፍተኛ ሁኔታ ማጋጠሙና እና የዉጭ ሀገር ባንኮች ወደ ሀገራችን እንዲገቡ መፈቀዱን ገልጸዋል፡፡

የንግድ ክፍያ ስርዓት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ኩባንያዎችና የቴሌኮም ኦፕሬተሮች ክፍት መደረጉ በሀገር ውስጥ ባሉትየባንኪንግ ኢንዱስትሪዎች መካከል ያለዉ ፉክክር በከፍተኛ ሁኔታ መቀጠሉ ብርቱ የሆነ ውድድር ውስጥ እንድንገባ አድርጎናል ብለዋል፡፡

ከውጭ ሀገር እና ከሀገር ውስጥ ባንኮች የሚጠብቀውን ውድድር አዋሽ ባንክ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣት ሁላችንም ዝግጁ መሆን ይጠበቅብናል ሲሉ አቶ ፀሐይ አሳስበዋል፡፡

በመጀመሪያው ግማሽ ዓመት በባንኩ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ዕቅድ አፈፃጸም ሪፖርት የቀረበ ሲሆን በሪፖርቱም የአምስት ዓመት የኮርፖሬት ስትራቴጂ ጥናት ተጠናቆ በሥራ ላይ እንዲውል በዳይሬክተሮች ቦርድ መወሰኑ ተገልጿል፡፡

የባንኩ የተከፈለ ካፒታል እ.ኤ.አ. ሰኔ ወር 2022 መጨረሻ ላይ ከነበረበት የብር 10.3 ቢሊዮን እ.አ.አ ሰኔ ወር 2027 መጨረሻ ላይ ወደ ብር 55 ቢሊዮን እንዲደርስ በባንኩ የባለ አክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የተወሰነ ሲሆን አዋሽ ባንክ አዲስ ከሚደለደሉት የባንኩ አክሲየኖች ውስጥ የሁለት ቢሊዮን ብር ዋጋ ያላቸው አክሲየኖች ለባንኩ ሰራተኞች እንዲሸጥ መወሰኑ በሪፖርቱ ተጠቅሷል

የባንኩ የደንበኞች የግንኙነት ማዕከልን (Contact Center) ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ በማስገንባት በአዲስ መልክ አገልግሎት እንዲሰጥ መደረጉን እና ማዕከሉ የሰራተኞች መዝናኛ፣ ካፍቴሪያ እና የተለያዩ ክፍሎች ያሟላ መሆኑን ከቀረበው ሪፖርት ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ለባንኩ ደንበኞች የሚሰጡትን አገልግሎቶች ለማዘመንና ደንበኞቹ ያለምንም ውጣ ውረድና ልፋት በአቅራቢያቸው እና በሚያመቻቸው የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት እንዲጠቀሙ ለማስቻል የአዋሽ ኢ ስኩል ማኔጅመንት ሲስተም ሥራ ላይ ውሏል፡፡ እንደዚሁም የአዋሽ ክሬዲት ካርድ ደንበኞች በንግድ ቦታዎች በዱቤ አሰራር ክፍያ እንዲፈጽሙ የሚያስችላቸው የክሬዲት ካርድ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል፡፡

በተመሣሣይ መልኩ በአሁኑ ጊዜ ባንኩ ከውጭ ሀገር ያስገባቸውን ከ1 ሺህ በላይ ዘመናዊ የኤቲኤም ማሽኖች በተመረጡ ቅርንጫፎች እና የንግድ ማዕከላት እየተተከሉ ሲሆን የኤቲኤሞቹ መጠለያ (Shade) ስራም እየተከናወነ ምሆኑ ተገልጿል፡፡



የላቀ ውጤት ያስመዘገቡ የቅርንጫፍና የሪጅን ተሸላሚዎች

በግማሽ ዓመቱ የባንኩን የተቀማጭ ሂሣብ እና የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለማሣደግ በርካታ ሥራዎች በመሰራታቸዉ ከ1.5 ሚሊዮን በላይ አዳዲስ ደንበኞችን ማፍራት የተቻለ ሲሆን፣ 75 አዳዲስ ቅርንጫፎችንም በመክፈት ለአገልግሎት ማብቃት መቻሉንና ከአዳዲስ ደንበኞችም ከብር 20 ቢሊዮን በላይ ተቀማጭ ሂሣብ የተሰበሰበ መሆኑን በሪፖርቱ ተመላክቷል፡፡

በሌላ በኩል አዋሽ ባንክ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ከመወጣት አኳያ የሥራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸውን ወጣቶች ለማበረታታት # ታታሪዎቹ የተሰኘውን የውድድር መርኃ ግብር ቀርጾ ውድድሩን በማካሄድ ላይ እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡

የባንኩን የፋይናንሻል አፈጻጸም እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 2022 መጨረሻ ላይ የባንኩ ጠቅላላ ተቀማጭ ሂሣብ ኤል ሲ ማርጅንን ጨምሮ ብር 173.12 ቢሊዮን መድረሱንና ይህም ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ51 በመቶ ዕድገት ያሳየ ሲሆን ካለፉት ዓመታት ዕድገቶች አኳያም ከፍተኛ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በመንፈቅ ዓመቱ ዕቅድ አፈጻጸም የዕቅዳቸውን 100% እና ከዚያ በላይ ላሳኩ 279 የባንኩ ቅርንጫፎች ዕዉቅና የተሰጠ ሲሆን በተመሣሣይ መልኩ እ.ኤ.አ እስከ ዲሴምበር 2022 መጨረሻ ላይ የተሰጣቸውን ዕቅድ በማሳካት የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ 34 ጀግና ቅርንጫፎች የማበረታቻ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

የውጭ ምንዛሪ ግኝትን በተመለከተ ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ25 በመቶ ዕድገት ወይም የ158.3 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጭማሪ በማሳየት እ.ኤ.አ ዲሴምበር 31, 2022 ላይ 783 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር መሆን ችሏል፡፡



የስብሰባው ተሳታፊዎች በከፊል

ከወጪ ንግድ፣ ከSWIFT እና ከውጭ ምንዛሪ ግዥ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ግኝት 100% ዕቅዱን ማሣካት የተቻለ ሲሆን ከውጭ ሀገር ሀዋላ የተገኘው የውጭ ምንዛሪ ከአምናው ተመሣሣይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ46 በመቶ ቅናሽ አሣይቷል፡፡ ምንም እንኳን የጥቁር ገበያው የምንዛሪ ዋጋ መናር ለውጭ ሀገር ሀዋላ ቅናሽ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ቢኖረውም፣ የደንበኞች አገልግሎታችንን በማሻሻል፣ የውጭ ሃገር የሃዋላ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ቁጥር በማብዛት እና የተለያዩ የማበረታቻ ስልቶችን በመጠቀም የሐዋላ ገቢን ማሣደግ እንደሚገባ አቶ ፀሐይ አሳስበዋል፡፡

የብድር አገልግሎትን በተመለከተ ባንኩ ለተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሰጠው የብድር መጠን ብር 158.2 ቢሊዮን የደረሰ ሲሆን ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር የ61 በመቶ ዕድገት አሣይቷል፡፡ በተለይ ለወጪ ንግድ (Export Sector) የተሰጠው ብድር የ24.6 በመቶ ዕድገት በማሣየት ብር 29.96 ቢሊዮን ደርሷል፡፡



የስብሰባው ተሳታፊዎች በከፊል

የባንኩ ጠቅላላ ገቢ ባለፈው ዓመት ተመሣሣይ ወቅት ከነበረበት ብር 9.8 ቢሊዮን የብር 3.8 ቢሊዮን ጭማሪ በማሳየት ወደ ብር 13.6 ቢሊዮን ማደግ ችሏል፡፡ ይህም ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት አንጻር የ40 በመቶ ዕድገት አሣይቷል፡፡ የባንኩ ጠቅላላ ወጪ ደግሞ የብር 2.9 ቢሊዮን ወይም የ55 በመቶ ዕድገት በማስመዝገብ ብር 8.2 ቢሊዮን መድረሱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የባንኩ ያልተጣራ ትርፍ እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 2022 መጨረሻ ላይ ብር 5.4 ቢሊዮን ሲሆን ይህም ከአምናው ተመሣሣይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ21 በመቶ ዕድገት ማስመዝገብ መቻሉ ተገልጿል፡፡

በቀረበው ሪፖርት ላይ በተደረገ ውይይት የመድርኩ ተሳታፊዎች በሰጡት አስተያየት በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ጥቃቅን ክፍተቶች መኖራቸው የተስተዋለ ቢሆንም እስካሁን በተገኘው ውጤት የባንኩ አቋም የተሻለ አፈጻፀም እንዳለውና መሪነቱን ለማስቀጠል ያሉትን ክፍተቶች በመሙላት የላቀ ውጤት ለማስመዝገብ በትኩረት እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

በመጨረሻም የስብሰባው ተሳታፊዎች ባለአስር ነጥብ የአቋም መግለጫ በማውጣት በቀጣይ ጊዜያት አቅማቸውን በማጠናከር እና በመተባበር ለ2022/23 ሂሣብ ዓመት የተቀመጡ ዕቅዶች መሉ በሙሉ ለማሳካት ከወዲሁ በቁርጠኝነት እንደሚሰሩ ቃል ገብተዋል፡፡

# አዋሽ ባንክ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ




የመግባቢያ ስምምነት የፊርማ ስነ ስርዓት

አዋሽ ባንክ ከኢትዮ ኢንጅነሪንግ ግሩፕ ጋር ለመስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ጥር 20 ቀን 2015 ዓ/ም ተፈራርሟል፡፡

የአዋሽ ባንክ ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ፀሀይ ሽፈራው በፊርማ ስነ ስርዓቱ ላይ እንደተናገሩት የስምምነቱ ዋና ዓለማ በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የነበረውን የስራ ግንኙነት እና አጋርነት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የሚያስችል ታሪካዊ ስምምነት መሆኑን ተናግለሯል።

የፊርማ ስነ ስርዓቱ በአዋሽ ባንክ እና በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ መካከል ያለው የስራ ትብብር በባንኩ ፖሊሲ እና በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ፍላጎት መሠረት ባንኩ ለኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ አስፈላጊውን የባንክ አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያደርግ እና ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ድርጅቶች በተለየ ሁኔታ ባንኩ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አክለውም አዋሽ ባንክ ለኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ድርጅቶች የብድርና የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እንዲሁም ለድርጅቱ አመራሮችና ሠራተኞች ባንኩ በአነስተኛ ወለድ ምጣኔ የብድር አቅርቦት እንደሚያመቻች አስረድተዋል፡፡

አያይዘውም በሁለቱ ተቋማት መካከል ያለው ግንኙት ይበልጥ የተሳለጠ እንዲሆን አዋሽ ባንክ በዋና መስሪያ ቤት ደረጃ የግንኙነት ስራ አስኪያጅ በአቅራቢያው ባሉ ቅርንጫፎች ደግሞ የግንኙነት ኦፊሰሮችን ለኢትዮ ኢንጅነሪግ ግሩፕ እንደሚመድብ ተናግረዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ጥያቄ መሠረት ሁሉንም የባንክ አገልግሎቶች በአቅራቢያቸው ያገኙ ዘንድ በተቋሙ ቅጥር ግቢ ወይም የተቋሙ ፕሮጀክቶች ባሉበት ቦታዎች ውስጥ አዋሽ ባንክ ልዩ ቅርንጫፎችን እንደሚከፍት እና ኤቲኤምችን እንደሚተክል ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ዋና ስራ አስፈጻሚ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ በበኩላቸው አዋሽ ባንክ በባንኪንግ አገልግሎት ያመጣው ልህቀት እና ባንኩ በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ ያለ በፈጠራ እና በፕሮጀክቶች ላይ ኢንቨስት ማድረግ የጀመረ መሆኑ ከባንኩ ጋር አብሮ ለመስራት ስምምነት ላይ መድረሳቸውን በመግለጽ የመግባቢያ ስምምነቱ የያዝናቸውን ተልዕኮ ለማሳካትና በጋራ አብሮ ለማደግ ያስችለናል ብለዋል፡፡



የመግባቢያ ስምምነት የፊርማ ስነ ስርዓት

በተመሳሳይ አዋሽ ባንክ ከኢትዮጵያ አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት እና ከኦርጋናይዜሽን ኦፍ ኢጁኬሽናል ኮኦፕሬሽን ጋር አብሮ ለመስራት የሚያስችለውን የመግባቢያ ስምምነት ተፈራርሟል፡፡የመግባቢያ ስምምነቱ አዋሽ ባንክ ለተቋማቱ አመራሮችና ሠራተኞች የውጭ ምንዛሬ አቅርቦትና በአነስተኛ ወለድ ምጣኔ የብድር አቅርቦት እንደሚያመቻች ተገልጿል፡፡



የመግባቢያ ስምምነት የፊርማ ስነ ስርዓት

# አዋሽ ባንክ በቦረና ዞን በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች 30 ሚሊዮን ብር ለገሰ

በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች በተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ችግሮች ሳቢያ ለተለያዩ ጉዳቶች ለሚጋለጡ ዜጎች ድጋፍ በማድረግ የሚታወቀዉ አዋሽ ባንክ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ቦረና ዞን በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች የሰላሳ ሚሊዮን ብር የካቲት 24 ቀን 2015 ዓም  ድጋፍ አድርጓል።

አዋሽ ባንክ ባለፈዉ ዓመትም በቦረና ጉጂ ዞኖች   በድርቅ ለተጎዱ ወገኖች የብር 60 ሚሊዮን ብር ለግሷል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በማህበራዊ ኃላፊነት መወጫ መርሐግብሩ በምዕራብ ኦሮሚያ ተከስቶ በነበረዉ የእርስ በርስ ግጭት ተፈናቅለዉ ለነበሩ ዜጎችና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ንፋስ ቀላቅሎ በጣለዉ ከባድ ዝናብ ቤት ለፈረሰባቸዉ አባወራዎች እንዲሁም በሱማሌ ክልል በተከሰተው ድርቅ ሳቢያ ለችግር ተጋላጭ ለሆኑ ወገኖች የገንዘብ እና የዓይነት ድጋፍ ማድረጉ ይታወሳል።

# አዋሽ ባንክ በተለያዩ የሀገራችን ከተሞች አዳዲስ ህንጻዎችን ሊገነባ ነው

አዋሽ ባንክ በቡራዩ፣ በወሊሶ እና በቢሾፍቱ ደረጃቸውን የጠበቁ ዘመናዊ አዳዲስ ህንፃዎች ሊያስገነባ ሲሆን የእነዚህ ህንጻዎች የአርክቴክቸራል ዲዛይን ውድድር አሸናፊ ለሆኑ ድርጅቶች ዕውቅና ሰጥቷል፡፡




የዕውቅና ስነ ስርዓት በከፊል

አዋሽ ባንክ በአዲስ አበባ የፋይናንስ ማዕከል በሆነው ስፍራ በራስ አበበ አረጋይ ጎዳና ላይ ባለ 18 ወለል ህንጻ የራሱ ዋና መስሪያ ቤትን በመገንባት ፈር ቀዳጅ ሲሆን በተጨማሪም ከአዲስ አበባ ከተማ ውጪ በተለያዩ የሀገራችን ዋና ዋና ከተሞች  የራሱን ግዙፍ ህንፃዎች ገንብቷል፡፡

ይህ የህንጻዎች ግንባታ የባንኩን የሀብት መጠን ከማሳደግ ጎን ለጎን ለከተሞች ዕድገትና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የራሱን አስተዋፅኦ በማበርከት ላይ ይገኛል፡

# ምልከታ

# ከቴክኖሎጂ ፎልደር...

ቀድሞ ያኔ ዓለም ሳይሰለጥን ጊዜው ሳይሻሻል ዘመኑ በቴክኖሎጂ ባልዘመነበት በዚያ ሰዓት የሰው ልጆች ጉዳያቸውን ለመከወን መውጣትና መውረድ ብዙ መድከም ይጠበቅባቸው ነበር፡፡ ዛሬ ዛሬ ለቴክኖሎጂ ምስጋና ይግባውና ዓለም መንደር በሆነችበት በዚህ ዘመን ብዙ መባከን ቀርቷል፡፡

በዘመነ ግሎባላይዜሽን በርካታ የቴክኖሎጂ ትሩፋቶች ተፈጥረው ህይወትን ቀላል እና ምቹ እያደረጉት ከመጡ ሰንበትበት ብለዋል፡፡ በዚህ ዘመን የባንክ ኢንዱስትሪው ከዘመኑ ጋር እየዘመነ ነገሮችን ቀላል እያደረገው ነው፡፡ ከእነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ደግሞ የክሬዲት ካርድ አንዱ ነው፡፡

### ለመሆኑ ክሬዲት ካርድ ምንድነው? አገልግሎቱንስ በምን መልኩ ነው ማግኘት የሚቻለው? እርስዎስ የክሬዲት ካርድ ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ? ጥቅም እና ጉዳቱስ?

## ክሬዲት ካርድ ምንድን ነው?

ክሬዲት ካርድ በፋይናንሺያል ወይም የባንክ አገልግሎት የሚሰጥ ትንሽ የአራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው የፕላስቲክ ወይም የብረት ቁራጭ ነው። የካርድ ክፍያዎችን በሚቀበሉ ተቋማት ውስጥ ምርቶችን እና ዕቃዎችን ለመግዛት ግለሰቦች ብድር እንዲሰጡ ያስችላቸዋል. ክሬዲት ካርዶች ደንበኞቻቸው የተበደሩትን ገንዘቦች ከማንኛውም አግባብነት ካለው ክፍያ ጋር፣ ከማንኛውም ተጨማሪ የጸደቁ ክፍያዎች ጋር ሙሉ በሙሉ በክፍያ ቀን ወይም በጊዜው እንዲከፍሉ ይጠይቃሉ።

ከተለመደው የክሬዲት መስመር ጋር በትይዩ፣ የክሬዲት ካርድ አቅራቢው ለተጠቃሚዎች ሁለተኛ የገንዘብ ክሬዲት መስመር ሊሰጥ ይችላል፣ ይህም በግል ብድሮች መልክ ገንዘብ እንዲበድሩ ያስችላቸዋል፣ ይህም በኤቲኤም ወይም በክሬዲት ካርድ መገልገያ ክፍያዎች። ዋናውን የክሬዲት ተቋም ከሚጠቀሙ ግብይቶች ጋር ሲነጻጸሩ፣ እንደዚህ ያሉ የግል ብድሮች ብዙውን ጊዜ እንደ የጥበቃ ጊዜ እና የወለድ ተመኖች ያሉ ልዩ መለኪያዎች አሏቸው።




የብድር ገደቦች በተለምዶ በአቅራቢዎች የሚወሰኑት በአንድ ሰው የብድር ብቃት ላይ በመመስረት ነው። ብዙ ድርጅቶች ደንበኞቻቸው በክሬዲት ካርዶች እንዲከፍሉ ይፈቅዳሉ ፣ ይህም ዛሬ የተለያዩ ዕቃዎችን / መፍትሄዎችን ለማግኘት በጣም ታዋቂ ከሆኑ የክፍያ ዓይነቶች አንዱ ነው።

# ስለ ክሬዲት ካርድ ምንነት ባለሙያዎች ምን ይላሉ?

የዩናይትድ ኪንግደም የተመሰከረላቸው የሒሳብ አዋቂዎች ማኅበር አባል የሆኑት አቶ ጥላሁን ግርማ ባንኮች በተለምዶ ሁለት ዓይነት የካርድ አገልግሎቶች እንደሚሰጡ ያስረዳሉ።

የማማከር እና ኦዲቲንግ ባለሙያው እንደሚሉት ዴቢት፤ ደንበኛው ባለው ተቀማጭ ገንዘብ መጠን ከኤቲኤም ወጪ ማድረግ የሚያስችለው፤ እንዲሁም በክፍያ ማሽን መጠቀም የሚያችለው ካርድ ነው።

"ነገር ግን ክሬዲት ካርድ ማለት ባንኩ 'ካለህ ተቀማጭ ገንዘብ በላይ ይህን መጠቀም ትችላለህ' ብሎ የሚፈቅድልህ ጊዜያዊ ብድር ነው።

ባንኮች ለደንበኞቻቸው ይህን የካርድ አገልግሎት የሚፈቅዱት የቀደመ የሒሳብ አጠቃቀም እንዲሁም የገቢ ምንጭ እና መጠናቸውን ከግምት አስገብተው ነው።

አቅም ላላቸው ደንበኞች ካላቸው ተቀማጭ ገንዘብ በላይ ወጪ ማድረግ እንዲችሉ ሊፈቀድላቸው እንደሚችልም ያስረዳሉ።

ባለሙያው የክሬዲትና ዴቢት ካርድ ልዩነት ሰርፆ እንዲገባን በምሳሌ ያስረዱናል።

ለምሳሌ ይላሉ. . . "20 ሺህ ብር ካለህ፤ ከኤቲኤምም አውጣ፣ ግብይትም ፈጽመበት፣ ካለህ በላይ ማውጣት አትችልም።"

ክሬዲት ካርድ ግን ባንኮች የደንበኛው መልሶ የመክፈል አቅም ከግምት በማስገባት ለአጭር ጊዜ የሚሰጥ ብድር ዓይነት ነው።

በበርካታ የዓለም አገራት የክሬዲት ካርድ ብድር ወለድ የሚከፈልበት ነው። ነገር ግን በአንዳንድ አገራት ደንበኞች በተሰጣቸው ቀነ ገደብ ካልከፈሉ ነው ወለድ የሚጣልባቸው።

"ለምሳሌ በ15 ቀናት ውስጥ እከፈላለሁ ብለህ ሳትከፍል ቀኑ ካለፈብህ ወለድ ይኖረዋል። የአዋሽ ባንክ ፖሊሲ ምን ሊሆን እንደሚችል የምናየው ነው የሚሆነው።"

# ካርዱን ለማግኘት ምን ያስፈልጋል?

ደንበኞች የክሬዲት ካርድ አገልግሎት ለማግኘት ለባንኩ ይህን ያህል ብድር ይፈቀድልኝ ብለው ማመልከቻ ማስገባት አለባቸው።

ባንኩ ባስቀመጠው መሥፈርት መሠረት የደንበኞችን አቅም እንዲሁም ከባንኩ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ተመልከቶ ፈቃድ ይሰጣል።

"የደመወዝ መጠንህ ሊሆን ይችላል፤ ከባንኩ ጋር ያለህ ግንኙነት ሊሆን ይችላል፤ ነጋዴ ከሆንክ የንግድ ሁኔታህ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ባንኩ ኪሳራውን እያወቀ ሊፍቀድ ይችላል።"

ባለሙያው ደጋግመው የባንክ ተጠቃሚዎች የክሬዲት ካርድን ዓላማ በግልፅ ማወቅ እንዳለባቸው ይመክራሉ።

"ክሬዲት ካርድ የሚሰጥህ ለአጭር ጊዜ የብድር ፍላጎትህ ነው። እንጂ ቋሚ ንብረት [መኪና፣ ቤት] እንድትገዛበት አይደለም።"

የክሬዲት ካርድ ዋነኛው ዓላማው ድንገተኛ ለሆነ የገንዘብ ችግር መውጫ ነው። ለዚህ ነው የሚመለስበት የጊዜ ገደብ የተቀመጠለት ይላሉ የምጣኔ ሃብት ባለሙያው።

"አዋሽ ባንክም የተጠቀምከውን ገንዘብ የምትመልሰው በምን ያህል ጊዜ ነው የሚለውን በተመለከተ የራሱን ፖሊሲ ያወጣል ብዬ አስባለሁ። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ይህ የሚወሰነው በደንበኛው የገቢ ምንጭ ነው።"

ለምሳሌ እርስዎ ተቀጣሪ ከሆኑ በወሩ መጨረሻ ደመወዝ ሲቀበሉ ለመክፈል ሊስማሙ ይችሉ ይሆናል፤ በንግድ ከተሠማሩ ደግሞ ምናልባት በወር ሁለት ጊዜ ለመክፈል ይፈርማሉ።

አዋሽ ባንክ በኢትዮጵያ የክሬዲት ካርድ አገልግሎት በመስጠት የመጀመሪያው ባንክ ለመሆን ችሏል። አዋሽ ባንክ በቅርቡ ይፋ እንዳደረገው 'ዴቢት ካርድ' ከተሰኘው አገልግሎት በተጨማሪ፣ የክሬዲት ካርድ አገልግሎት መስጠት ጀምሯል።

በዚህም ሁለት ዓይነት የክሬዲት ካርድ አገልግሎት እንደጀመረ በገለጸበት ወቅት አንደኛው ሙሉ በሙሉ በአንድ ጊዜ የሚመለስ፣ ሌላኛው ደግሞ ተከፋፍሎ የሚመለስ ነው ብሏል።

የኢትዮጵያ ባንኮች ከዴቢት ካርድ አገልግሎት በቀር ሌሎች የካርድ አገልግሎቶች ለደንበኞቻቸው አይሰጡም።

አብዛኞቹ ዓለም አቀፍ ባንኮች የዴቢት ካርድን ጨምሮ የክሬዲት ካርድ እንዲሁም ሌሎች የካርድ አገልግሎቶች ለደንበኞቻቸው ይሰጣሉ።

# የክሬዲት ካርድ ጥቅምና ጉዳቱ

የ44 ዓመቱ እንግሊዛዊ ዳረን የ32 ሺህ ዩሮ ዕዳ ውስጥ ከገባ በኋላ የሚያደርገው ጠፍቶት ነበር።ዳረን ከባንክ የወሰደውን ክሬዲት ካርድ ለሚያስፈልገው ጉዳይ ጥቅም ላይ ቢያውለውም ዕዳውን በጊዜ መክፈል የሚያስችል አቅም አልነበረውም።

"እንኳን ልቀንስ ይቀርና በዕዳ ላይ ዕዳ ስጨምር ነው የከረምኩት። ከወር ወር ሲያድግ፤ ከዓመት ዓመት እዳዬ ሲያሻቅብ ነው የከረመው። በጣም ጭንቀት ውስጥ ነበርኩ።"

ምንም እንኳ ዳረን አሁን ዕዳውን ከፍሎ ቢገላገልም በርካታ እንግሊዛዊያን አሁንም የክሬዲት ካርድ ዕዳ ውስጥ ናቸው።

አቶ ጥላሁን እንደሚሉት ክሬዲት ካርድ በአግባቡ ጥቅም ላይ ካልዋለ ተጠቃሚውንና ባንኮች ለኪሳራ ሊዳርግ ይችላል። ለዚህ ነው የክሬዲት ካርድ ዋነኛ ዓላማው መሆን ያለበት አንድን ችግር ወዲያው ለመፍታት መሆን አለበት የሚሉት።

"ለምሳሌ ቤተሰብ ቢታመምብህ አሊያም በሚቀጥለው ወር ዕቁብ የሚወጣልህ ቢሆንና አሁን አንድ ዕቃ መግዛት ብትፈልግ ክሬዲት ካርድ መጠቀም ትችላለህ።"

ባለሙያው ክሬዲት ካርድ ማለት "ልክ እንደ ቴሌ ብር ነው" ይላሉ። "ቴሌ ገንዘብ ሳይኖርህ ሲቀር የብድር አገልግሎት ይሰጥሃል። በሚቀጥለው ስትሞላ ከሒሳብህ ላይ ይወስዳል።"

በውጭው ዓለም 'ክሬዲት ስኮር' የሚባል ሐሳብ አለ። የክሬዲት ስኮር ማለት አንድ ሰው ብድር ወስዶ የመመለስ ታሪኩ እንዴት ያለ ነው የሚለውን የሚያሳይ ነው።

ብድር ወስደው በጊዜ የሚመልሱ ሰዎች መልካም 'ክሬዲት ስኮር' ያላቸው ተብለው ይጠራሉ። የክሬዲት ታሪካቸው ጥሩ የሆኑ ሰዎች በባንኮች ዘንድ ይከበራሉ፤ የሚፈልጉት ጉዳዩ በቶሎ ይሳልጥላቸዋል።

በአብዛኛዎቹ አገራት የክሬዲት ካርድ ወለድ፣ የባንኮች ለደንበኞቻቸው ከሚሰጧቸው ሌሎች ካርዶች ወለድ ከፍ ያለ ነው።

"ብድር ስለሆነ ወልድ አለው። አደጋ ስላለው ነው ወለዱ ከፍ የሚለው። ንብረት አስይዞ የሚወስድ ሰው እና ንብረት ሳያስዝ ብድር የወሰደ ሰው እኩል ስላልሆነ የወለድ መጠኑን ከፍ በማድረግ ነው ስጋቱን የሚያጣጡት።"




# ትንሽ ስለክሬዲትና ዴቢት ካርድ ልዩነት

ዴቢት ካርድ ሲጠቀሙ ቀረጥ የሚጥል የግል ማሽን [ኤቲኤም፣ የግብይት ማሽን] ካልሆነ በቀር ተጨማሪ ክፍያ አይከፍሉም። አልፎም ለተጠቀሙበት ክፍያ ካለው ቀድሞ ያሳወቆታል።

ወደ ክሬዲት ካርድ ስንመጣ ግን ከኤቲኤም ማሽን ገንዘብ ሲያወጡ ክፍያ ይከፍላሉ። አንዳንድ ጊዜ ካርዱን የሰጠዎት ባንክ የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል።

በበይነ መረብ ዕቃና አገልግሎት የሚሸጡ ድርጅቶች ከዴቢት ካርድ ይልቅ ክሬዲት ካርድ ይመርጣሉ። ለዚህ ምክንያቱ ክሬዲት ካርድ ሲሆን ገንዘቡን ከባንክ ቀጥታ ማግኘት ስለሚችሉ ነው።

ባለሙያዎች ክሬዲት ካርድ ተጠቅሞ ከኤቲኤም ገንዘብ ማውጣትን አይመክሩም። ከዚያ ይልቅ በሚገበያዩበት ወቅት ክሬዲት ካርድዎን ይጠቀሙ ይላሉ።

ቪዛ፣ ማስተርካርድ፣ አሜሪካን ኤክስፐረስ እና ዲስከቨር የክሬዲት ካርድ ኔትዎርኮች ናቸው። ባንኮች እነህን ኔትዎርኮች ተጠቅመው ነው ለደንበኞቻቸው ክሬዲት ካርድ የሚያውጁት።

አብዛኞቹ ዓለም አቀፍ ባንኮች የክሬዲት ካርድ ለሚጠቀሙ ደንኞቻቸው ማበረታቻ ሽልማት ይሰጣሉ።

ለምሳሌ የአውሮፕላን ቲኬት ለመቁረጥ፣ ለሆቴል ክፍያ፣ ለበይነ-መረብ ግብይት ክሬዲት ካርድ ከሚጠቀሙ ደንበኞቻቸው ማበረታቻ ይሰጣሉ። ማበረታቻው በአየር መንገድ ማይል፣ በተጨማሪ የሆቴል ክፍያ እንዲሁም በስጦታ ካርድ መልክ ሊሰጥ ይችላል።

ባንኮች ለደንበኞቻቸው በየወሩ 'ስቴትመንት' [የባንክ ሒሳብ መረጃ] ይልካሉ። ይህ ስቴትመንት ደንኞች ክሬዲት ካርዳቸውን ተጠቅመው ምን ያህል ክፍያ እንደፈፀሙ፣ የወለድ መጠኑን እና ተጨማሪ ክፍያውን የሚያካትት ነው።

አክሎም፤ ክሬዲት ካርዳቸው ውስጥ ምን ያህል ገንዘብ እንደቀረ፤ መልሰው ሊከፍሉ የሚገባቸው ዝቅተኛ መጠን ስንት እንደሆነ እና እንዴት መክፈል እንደሚችሉ ይካተትበታል።

ጽሁፉን ስናዘጋጅ ቢቢሲ አማርኛ ዜናን በዋቢነት ተጠቅመናል

# Wastina Be Kiso! (ዋስትና በኪሶ)
# Awash Credit Card

In today's world, the world where it is quite difficult to fill every aspect of our needs, it is so important to have an organization that offers credit card. In the history of Ethiopian banking, Awash Bank is the first bank that unveils credit card to its esteemed customers. According to statistical data, there are more than 2.8 billion credit card users globally and of this United States of Amerika, Canada, United Kingdom, Japan and Germany are the tops five countries with active credit card users. However, in our country, there is no any other bank that unveils credit card till Awash Bank. In order to ease the inflation and difficultness of life in our country Ethiopia, Awash Bank launched a credit card that named "Wastina Be Kiso ((ዋስትና በኪሶ)-Awash Credit Card.

To define, credit card is a thin rectangular piece of plastic or metal issued by a bank or financial services company that allows cardholders to borrow funds with which to pay for goods and services with merchants that accept cards for payment or withdraw cash via ATM or Branch POS in the form of Cash advance. Credit cards impose the condition that cardholders pay back the borrowed money, plus any applicable interest, as well as any additional agreed-upon charges, either in full by the billing date or over time.

In understanding the recent developments that indicate the feasibility and in demand of the card in Ethiopia, Awash Bank is introducing Credit Card Services. The Credit cards aims to provide an efficient means of getting cash and making payments where the normal financial systems and services cannot meet specific requirements for expenditures and it is for all customer types who can meet the criteria and due diligence tests.

At this introductory stage of the credit card product, the Bank plans to issue the credit cards with closely similar natures without significant differentiation to all customers except the variation in credit limits. The credit cards for personal customers as well as for corporate customers can be granted with free of any collateral requirement. With this Card, the Bank grants a client to utilize funds up to the maximum limit or pre-approved limit given by the Bank and make payments at Merchant locations, POS terminals withdraw cash from ATM and POS terminals based on the type of the services subscribed by the cardholder, subject to the approval of the Bank.

Here accordingly, there are two types of proposed credit cards. The first one is Charged credit card, type of Credit Card whereby customers are required to effect the whole amount of the utilized amount on the cycling date and keep on using the card until expiry date of the card and the next one is Revolving credit card, type Credit Card by which customers are required to effect some percentage on the utilized amount on instalment/monthly basis. The daily transaction limit of credit card is the same to debit card, 5000 at one time, 10,000 per day, 150,000 for daily purchasing via POS, and 50,000 for POS withdrawal per day.


n conclusion, as we have 'ዋስትና በኪሶ' why we face difficulties? Awash Bank, the leading private bank in Ethiopia and the Bank that always cares for its steamed customer and society has launched a credit card services and provided to any individual. So, have your credit card from the nearest branch of Awash Bank and make your life easier.




Source Awash Bank Card Banking Directorate

# እፍታ

Awash BIRR
Banking Everywhere




## ተላከኝ!

ተላከኝ ዋሌቴ ተላከ አዋሽ ብሬ፤
ሳልወጣና ሳልወርድ ሳልደክም በእግሬ፤
አለኝ ብዙ ጉዳይ አለብኝ ቀጠሮ፤
የማከናውነው በዕለት ተዕለት ኑሮ፤
የሂሳብ ጥያቄ የሞባይል ቢሉ፤
ክፍያ መፈጸም ገንዘብ መቀበሉ፤
ምንዛሬ ተመን መገበያየቱ፤
የስራዬ ብዛት እረ ስንቱ ስንቱ፤
የቱን አስፈጽሜ የቱን እተዋለሁ፤
ሀሳቤን በሙሉ ባንተ ላይ ጥያለሁ፤
ሁሉን ከውናለሁ ሆኜ አንድ ቦታ፤
ወጪ ሳላወጣ ስራዬን ሳልፈታ፤
አዋሽ ብሬ!
ነህና አጋሬ።

በሲሳዩ ነጻ (ሲስኮ) ከማርኬቲንግና
ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ANDROID APP ON Google play
Available on the iPhone App Store

አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

# የሰው ነገር
# በችሎት ፊት

አንድ ሲራራ ነጋዴ መንገድ ሲሔድ ቆይቶ ቀን በምሳ ሰዓት ከአንድ ዛፍ ሥር አረፍ ብሎ ምሳውን ቆሎ ቆርጥሞና ውሃ ጠጥቶ ጉዞውን ሲቀጥል ሁለት መቶ ጠገራ ብር ረስቶ ሄደ።

አንድ ገበሬ አግኝቶለት ያንን ገንዘብ ሊሰጠው ከኋላ እየሮጠ ተከተለውና ‹‹ሰውዬ ቆም ብለህ ጠብቀኝ፤ ጥለኸው የሔድከው ገንዘብህን አግኝቼልሃለሁ፤›› አለው። ነጋዴውም ‹‹ያገኘኸው ገንዘብ ስንት ነው?›› ሲለው ‹‹ሁለት መቶ ብር›› አለው።

ነጋዴው ግን ‹‹እኔ የጠፋብኝ ገንዘብ ሦስት መቶ ብር ነው። አንዱን መቶ ብር የት ደብቀህ ነው ሁለት መቶ ብር የምትሰጠኝ። ሞልተህ ካላመጣህ አልቀበልህም እከስሃለሁ። እንዲህ በዋዛ አንላቀቅም›› አለው።

ገበሬውም ገንዘቡን እንደያዘ ወደ ኋላ ተመለሰ። ነጋዴው የመሠረተው የውሸት ክስ በይግባኝ ተይዞ ወደ አፄ ቴዎድሮስ ሲቀርብ የሁለቱን አባባል ካዳመጡ በኋላ ነጋዴውን ምን ያህል ገንዘብ ነው የጠፋህ? ሲሉት ‹‹ሦስት መቶ ጠገራ ብር ነው›› አላቸው።

ገበሬውንም ‹‹ምን ያህል ገንዘብ አገኘህ?›› ሲሉት ‹‹ሁለት መቶ ጠገራ ብር ብቻ ነው›› አለ።

ከዚያ በኋላ ‹‹አንተ ነጋዴው ጠፋብኝ የምትለውን ሦስት መቶ ብር ከጣልክበት ቦታ ፈልገህ አግኝ። ሁለት መቶ ብር ያገኘኸው ገበሬ ደግሞ ሁለት መቶ ብር ጠፋኝ የሚል ሌላ ሰው እስከሚመጣ ድረስ ራስህ ልትጠቀምበት ትችላለህ›› ሲሉ ፈርደው ፋይሉ ተዘጋ። ምንጭ መክብብ አጥናው ‹‹የአባቶች ጨዋታ›› (2005)

# PROVERBS

Never spend money before you have it. -Thomas Jefferson

Save for a rainy day! – Aesop

If you buy what you don't need, you steal from yourself! – Swedish

A penny saved is a penny earned! – George Herbert

Interest on debt grows without rain.- Yiddish

The journey of a thousand miles begins with one step! - Lao Tzu

The habit of saving is itself an education; it fosters every virtue, teaches self-denial, cultivates the sense of order, trains to forethought and so broadens the mind. T.T Munger

The art is not only making money, but also in saving and investing it-

Save money and money will save you! Jamaican

Spending is quick; earning is slow. – Russian

Don't blame your income for the fact that you're not saving money.



Source: https://graciousquotes.com/saving-money/

# QUOTES

"Focus on all four of your net worth factors increasing your income, increasing your savings, increasing your investment returns and de-creasing your cost of living by sim-plifying your lifestyle." T. Harv Eker

"Saving is a commitment not an amount!" -Todd Christense

"The real measure of your wealth is how much you'd be worth if you lost all your money!" – Anonymous

"Do not save what is left after spending; instead spend what is left after saving." – Warren Buffett

"Try to save something while your salary is small; it's impossible to save after you begin to earn more." –Jack Benny

"Never depend on single income. Make investment to create a second source."- Warren Buffett

"Too many people spend money they earned...to buy things they don't want...to impress people that they don't like" -Will Rogers



"I believe that thrift is essential to well-ordered living. – John D. Rockefeller

"It is never too early to encourage long-term savings." - Ron Lewis

"Being a smart shopper is the first step to getting rich"- Mark Cuban

"It's not how much money you make, but how much money you keep, how hard it works for you and how many generations you keep it for" Robert Kiyosaki

"Small amounts saved daily add up to huge investments in the end" Margo Vader

"Save money on the big boring stuff so that you have something left over for life's little pleasures" Elisabeth Leamy

"It is thrifty to prepare today for the wants of tomorrow" Aesop

"Beware of little expenses; a small leak will sink a great ship!" Benjamin Franklin

Source: https://www.forbes.com/sites/robert-berger/2014/04/30/top-100-money-quotes-of-all-time

# Photo Reel











Architectural Design Competition Award for Burayu, Bishoftu and Woliso Building




Architectural Design Competition Award for Burayu, Bishoftu and Woliso Building

# The LEADING

Private bank
In Ethiopia



አዋሽ ባንክ
AwashBank
Nurturing Like the River

8980
www.awashbank.com